አማራ ባንክ
AMHARA BANK
ከባንክ ባሻገር!
Beyond Financing!

## አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር

## የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የጉባዔ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀፅ 366 (1) ፣ 367 (1 እና 2) ፣ አንቀፅ 372 እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ አንቀፅ 20 መሰረት የአማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 3ኛ ዓመት መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ታህሳስ 01 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ አዲስ ፓርክ ዴቨሎፕመንትና ማኔጅመንት ኃ.የተ.የግል ማህበር (ሚሊኒየም አዳራሽ) ይካሄዳል።

በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. **ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች**
   - 1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፡-
     - ✓ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 8፣ ለገሃር መብራት - አመልድ ሕንጻ ከ16-25ኛ ፎቅ
     - ✓ ስልክ: የጥሪ ማዕከል: 690 ፖ.ሳ.ቁ: 28450 ኮድ 1000
     - ✓ ድረ ገጽ: https://amharabank.com.et/
   - 1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- **MT/AA/3/0052689/2014**
   - 1.3 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- **6,516,327,000.00**
   - 1.4 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- **6,516,327,000.00**
2. **የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች**
   - 2.1 የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ ፣
   - 2.2 የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅ እና አዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል ፣
   - 2.3 እ.ኤ.አ የ2023/2024 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ፤
   - 2.4 እ.ኤ.አ የ2023/2024 የባንኩን የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ማድመጥና ማፅደቅ፤
   - 2.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እ.ኤ.አ የ2023/2024 ዓመታዊ የስራ ዋጋና እ.ኤ.አ የ2024/2025 ወርሃዊ አበል በሚመለከት በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
3. **ማሳሰቢያ**
   - 3.1 በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ህግ አንቀፅ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆን እና ድምፅ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።
   - 3.2 የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

**የአማራ ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**